ባለ እዳው ጎረቤቴ

መኖሪያችን ሸዋ -በሸን ማርያም አጥቢያ
ከአምባ ሥላሴ አልፎ- ከተራራው ወዲያ
አንድ ሰው ነበረ
በችግር የኖረ
ጥማድ በሬ ቢያጣ- ማሳው ቢያድርበት ጦም
በጥብቅ ለመነኝ- በድንግል ማርያም ስም
አልኩት ይህንን ሰው-በሬወቸን ተዋስ
ወስደህ ጥመዳቸው- ማሳህንም እረስ
ክረምቱን ይረሱ- ለቢጋም በወቅቱ
ተጠቀምባቸው- ደግሞም ለመውቃቱ

መጋቢት በቆሎ-ግንቦት ባቄላውን
ሰኔ ላይ ቦረቦር-ሃምሌ ላይ ደባዩን
እስከ ቡሄ ድረስ -ዘራራና ጤፉን
ስንዴውን -ነሃሴ-መስከረም -ሽምብራ- ዘራና ምስሩን
አረሙን አርሞ-ሰብስቦና ወቅቶ
ልጠይቀው ስሄድ-እርሱ ቤቱን ዘግቶ

አላየሁም አለኝ- ደግሞስ የምን በሬ
“እንደ እኔ ዓይነት ጀግና- ታታሪ ገበሬ
በሬወቹን ወስደህ-በምን ላርስልህ ነው
አስር ቤተሰቤን ምን ላበላልህ ነው
ዳኛ ይለየናል- ፍርድ ቤት ተሟገተን
ይለኝ እንደሆነ- በተሰቤን በትን”

ደግሜ አስለመንኩት- በወገን በባዳ
ዛሬ መልስ ላከ- እንዳለብኝ እዳ
“አበድሬው ነበር- እጥፍ ድርብ ጉብረት
ባለፈው ዓመት ላይ-መመለስ ያለበት
እኔ ስላልጠየኩ- አምጣ ስላላልኩት
እዳውን የተውኩት- ምነው የመሰልኩት”
ብሎ ነገራቸው ለሽማግሌወች- ለእነአባ ብላታ
ለካ እኔ የማላወቀው- “አለብኝ” ውለታ።

እንግዲህ ከሻትኩኝ -ሁለቱን በሬወች
ይካካሱ ሊል ነው- ተመልከቱ ሰወች
ምንድን ነው ጉብረቱ-ያበደርከኝ ብለው
“ባለወርቀ ዘቦ- ስድስት ክንፍ ያለው
በአልማዝና በእንቁ- ክፍክፉ የደራ
በእውቅ ባለሙያ- ሰሜን የተሰራ
አልማዙ ሃምሳ ኪሎ- እንቁው ሰባ እሚሆን
ከሰሜን የመጣ-በአፄ ናዖድ ዘመን
ከግራኝ አህመድ- ከዮዲት ቃጠሎ
ከዛግዌ ግዛት- ከነጭ ተሰውሮ
እንግሊዝ ሳይጭነው-ጣሊያንም ሳይዘርፈው
መንግስቱ ሳይወርሰው- ለዘር ዘር የቆየው
ትልቅ ጉብረቴ ነው
አለና መለሰ
መቸም ዛሬ ጉድ ነው
ምንድን ነው ስያሜው- የሃብትህ ዝርዝሩ

ብለው ሽምጋዮቹ- ብዙ ቢሞክሩ
መልስ አልነበረውም- እርሱም አያውቀውም
የእኔን ሃብት -መካዱን -ፍፁም ባያቆምም
ሚስቱ እምታቦካው- ዱቄት ያልነበራት
ልጆቹ የሌላቸው- ቁርስ ምሳና እራት
እንዲህ ያለ ንብረት-በእጁ ያልነበረው
የሰውን ውለታ ቆፍሮ ቀበረው
እንዲህ ያለው ዋሾ- የዲያብሎስ ፈረስ
በጣም አስቸገረ- አንዱ ለአንዱ እንዳይደርስ።

ደሳለኝ በርሄ
desberhe@gmail.com